# ብአዴን ባንዳ ነው!



ተምች ደም ለመምጠጥ ከአፉ የተኮሰው፣
ባማራ ገላ ላይ ክስክስ ያደረገው፣
የጊንጦች መንደፊያ ብአዴን ሰንኮፍ ነው፡፡

ባንዳ እያበላለጥክ የምትጎሻሸም፣
ተዝንጀሮ ቆንጆ ልትመርጥ የምታልም፣
ስትቃኙ አትደር እሩብ ባንዳ የለም፡፡

ለገሰ ፈብርኮት አብዮት የገዛው፣
ከከርስ በስተቀር አሞት ልብ የሌለው፣
ለሰላሳ ዓመታት አማራን ያስብለው፣
ብአዴን ‘አመራር’ ጠቅላላ ሎሌ ነው፡፡

ስታስጌጠው ብትውል ጀግና ልታደርገው፣
ሊፕስቲክ ከንፈሩን ሶስት ዙር ብትቀባው፣
ብአዴን የሚባል ሁሉም አሳማ ነው፡፡

ትናንትናም ወይ ጉድ ዛሬም እየየ ነው፣
አሽከር እየመራህ ዘራፍ ልትፎክር ነው?

ብንወቅር ብናፋጭህ አልተባህ አልሰላህ፣
ብአዴን ሎሌ ነው እያልን ብንመክርህ፡፡

ደጋፊዎቻቸው ብታምኑም ባታምኑም፣
እንዲህ ዓይነት ገረድ ጠላት የሚመግብ፣
በአማራ ምድር ላይ በቅሎበት አያውቅም፡፡

ዛፎችን ያስፈጀ ጠማማ ወዳችሁ፣
እጀታን ከዘራ ምርኩዝ ያረጋችሁ፣
ከሕዝብ ተጨማሪ እግዜር ይይላችሁ፡፡

በልቶ እማይጠግበው ተምች አገር የዘረፈው፣
አምስት ሚሊዮን ሕዝብ ከምድር ያጠፋው፣
ብአዴን ባንዳውን ሰንኮፍ አድርጎ ነው፡፡

ለሃያ አምስት ዓመት አበሳውን ያየው፣
አማራ አለወትሮው አንገቱን የደፋው፣
ብአዴን የሚባል እርጉም ደቅሎ ነው፡፡

እነ አሰፋ ማሩ መንገድ የወደቁት፣
እነ አስራት ወልደየስ ከመቃብር የገቡት፣
እነ ሳሙኤልም ባጭር የተቀጩት፣
እነ ጎቤ መልኬ በረሃ የቀሩት፣
ብአዴን ለጠላት እያበራ መብራት፡፡

ባህርዳር ወልዲያ ወጣቱ ያለቀው፣
አምባ ጊዮርጊስም ህፃን የረገፈው፣
ከብአዴን ቢሮ ስናይፐር ሰፍሮ ነው፡፡

ተራራ ሜዳውን ሌባ የሰረቀው፣
የሊጥ ዕቃ ሳይቀር ተዘርፎ ያለቀው፣
ከሀዲው ብአዴን እያቀበለ ነው፡፡

ሽፈራው ሽጉጤ ዘጸአት ያወጀው፣
ሆዳሙ ብአዴን አብሮ እየበላ ነው፡፡

ስንት ወይዛዝርት ለአረብ ገረድ የተሸጠው፣
ስንቱ በአገሩ ውስጥ በስደት የኖረው፣
ስንት ጎበዝ ከወህኒ በሳት የነደደው፣
ብአዴን ጉልቻ አማሳይ ሆኖ ነው፡፡

ዛሬም ያማራ ልጅ ወህኒ ቤት የሚያድረው፣
ብአዴን ለፓስተር ዲያቆኑ ሆኖ ነው፡፡

የአማራ ዘር ፍጅት እየከፋ ያለው፣
ፋኖ በብአዴን እጅ እግሩን ታስሮ ነው፡፡

የምትነታረክ ሽንጥህን ገትረህ፣
አንደኛውን ሎሌ ከሌላው አብልጠህ፣
ያስፈጇቸው አጥንት እሾህ ሆኖ ይውጋህ፡፡

አማራ ተዳር ዳር ምከር ተመካከር፣
ብአዴን ተጉያህ ተጣብቆ እንደ መዥገር፣
እንኳን ቆመህ ልትሄድ በክብር አትቀበር፡፡

የትግል መስመሩን ባንዳ እያሰመረው፣
ሕዝብ ነፃ ወጥቶ የሚያውቀው መቼ ነው?

ወጣት ሆይ ከትመህ አሳሪህን ታገል፣
ባንዳ በመለካት ጊዜህን አትግደል፣

ወጣት እንደ አያትህ ጎራው በል አጉረምርም፣
ታራጆችህ ገንዳ የሚልስ የሰው ደም፣
ባንዳ መሪህ ሆኖ ተክብርህ አትኖርም፡፡

*በላይነህ አባተ (abatebelai@yahoo.com)*
*ሐምሌ ሁለት ሺ አስራ አንድ ዓ.ም.*